# መታሰቢያ

ናፍቀው ነበረ ለማየት
ዘመድ፥ ወገን፥ ልጅ፥ ጎረቤት
እናት፥ አባት፥ ቤተሰብ
የተወለዱባትን መሬት
ጓጉተው ነበረ በእጅጉ
ቦሌ ማረፊያው እስኪደርሱ
ያገራቸውን ውሃ እስኪቀምሱ
እንጀራዋን እስኪጎርሱ
የቋጠሯትን ጥሪት ለወገን እስኪያቋድሱ
ጓጉተው ነበረ . . .
ደግሞ ም ነበሩ እነዚያ
የአገር ጌጦች፥ የአገር መኩሪያ
የሰንደቃችን አድማቂዎች
የማንነታችን ምልክቶች
በበረራ፥ በመስተንግዶ
ምስጉን፥ ትጉህ፥ ታታሪዎች
የኢትዮጵያ አየር መንገድ
አንጸባራቂ ኮከቦች።
ዕጣቸው ተገናኝና መንገዳቸው ሊገጣጠም
ሃሳብ፥ ምኞት፥ ዕቅዳቸው ላይሳካ፥ ላይፈጸም . . .
ፊታቸውን ወደ ኢትዮጵያ
ምኞታቸውንም እሷው ላይ
በተስፋ ተሞ ልቶ ነበር
ዐይናቸው አገር፥ ዘመድ ሊያይ።
ቤይሩት ግን . . . ቤይሩት ግን ጨከነችና
«ፈቃድ አልሰጥም» ብላቸው
ያገሬን ልጆች ሳትመልስ
ከደጇ አስቀረቻቸው።
ሕልማቸው በአየር ላይ ተንሳፍፎ
በጎዋ ላይ ተበትኖ
በሜዲትሬንያን ተውጦ
ልፋት፥ ድካማቸው ባክኖ
ጠፉ ያገሬ ልጆች ወትሮም አልተመቻቸው
«ዐረብ አገር» እየሳበ «ዐረብ አገር» ቀጠፋቸው።
ምነው እህቶቼ ቀራችሁ?
ቀይ ባሕር እንኳን ሳትደርሱ
ኢትዮጵያን ከቅርብ ሳታዩ
አየሯን ሳትተነፍሱ?
ምነው?!
ለነገሩ . . .
ምን ዋጋ አለው አሁንማ
የአምላክ ፈቃድ ተፈጽሟል
ነፍሳችሁን ይማርልን
ሙሉ ኢትዮጵያም ከልብ አዝኗል
ግን . . .

ጎልፈታችሁ ከንቱ አይደለም
ጥሎ ሄዷል ትልቅ ነጥብ
በ«ዐረብ አገር» የጠፉትን
ብዙ እህቶች እንድናስብ።
ወላጅ እናት አገር ቤት ሀብት
ወገን፥ ዘመድ፥ መከበሪያ
ችግር፥ ኀዘን፥ ጥም ተካፋይ
የጥቃት ጋሻ መከለያ
ናፍቃችሁ ነበር ለማየት
ዘመድ፥ ወዳጅ፥ ጓደኛ
ተሳቀቀ ወገናችሁ
አትኖሩምና ዳግመኛ።
መንገደኛ ወደቤቱ ይመለስ ነበር ለልማዱ
የሕዝብ ልብ ተሰበረ ያለቦታችሁ ብትወርዱ!
ነፍስ ይማር!
ሌላማ ምን ይባላል?
ነፍስ ይማር!
የእናንተንም፥ የሌሎቹንም የሁሉንም መንገደኞች
ነፍሳቸውን ይማርልን ይጽናኑልን ቤተሰቦች።
የሰው ዘር ናቸውና ክቡራን የፈጣሪ ልጆች
ኀዘናችን ይድረስልን ለሁሉም አገር ዜጎች።
ነፍስ ይማር!
ያገሬ ልጆች መጥፋት ቢያስጨንቀኝ፥ ቢያሳዝነኝ
እንደወጡ መቅረታቸው እያባባ ቢያስተክዘኝ
ነው እንጂ . . .
ሁሉም አይደሉ?
እንደወጡ የቀሩ?
ካሰቡበት ሳይደርሱ
የጠለፋቸው ባሕሩ?
ቢሆንም . . .
ወገኖቼ ያገር ልጆች
ተሳፋሪ መንገደኞች፥ የበረራ ባለሚሎች
የማንነቴ ተጋሪዎች፥ የእኔነቴ ተካፋዮች
ተስፋቸው፥ ሕልማቸው፥
ፍርሀታቸው፥ ጭንቀታቸው
ምኞታቸው፥ ሀሳባቸው፥
ድካመታቸው፥ ብርታታቸው . . .
ለልቤ ቅርብ ነውና የሕልውናቸው መሠረት
በእጅጉ አሳዝኖኛል የእነርሱ ወጥቶ መቅረት።
ብርታቱን ይስጥልን ለቤተሰብ፥ ለዘመድ፥ ወዳጅ ጓደኛ
የሁሉም መልካም ትዝታ ይሁንላችሁ መጽናኛ።

---

ቴዎድሮስ አበበ
Springfield, VA
የካቲት ፪ ቀን ፳፻፪ ዓ.ም. | February 9, 2010

(ከቤይሩት ወደ አዲስ አበባ ለመጓዝ እንደተነሣ ሜዲትሬንያን ባሕር ላይ ለወደቀው የኢትዮጵያ አየር መንገድ አውሮፕላን መንገደኞችና የበረራ ሠራተኞች፥ ለቤተሰቦቻቸውም ጭምር፥ ከጥልቅ ኀዘንና ከመልካም ምኞት ጋር የተበረከተ።)